# ጥገኝነት ለማግኘት ያቀረቡት ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ በኋላ ምን ይሆናል?

በኔዘርላንድስ ጥገኝነት እንደማይሰጥዎት IND ለእርስዎ አሳውቆዎታል። ይህ ለእርስዎ መጥፎ ዜና እንደሆነ እንረዳለን። ከኔዘርላንድስ እንድትወጡ በደንብ ማዘጋጀት የእኛ ስራ ነው። ይህንን እንዴት እንደምናደርግ የሚወሰነው እርስዎ እንድትመሰሉ ውሳኔ የተሰጥዎት ከሆነ ወይም ያልተሰጥዎት ከሆነ ነው። በሁለቱም ሁኔታዎች የእርስዎ ትብብር አስፈላጊ ነው።



## እንድትመሰሉ ገና ውሳኔ ያልተሰጥዎት ከሆነ

ከእሳቸው ጋር ልያኖርዎት የሚችሉ ቤተሰብ ወይም የምታውቃቸው ሰዎች ካሉ ከርስዎ ጋር ኣብረን እናጠናለን። ይህ ካልተሳካ ደግሞ መጠለያ ልንፈልግ እንችላለን። ይህ ጥናት 1 ዓመት ሊወስድ ይችላል። ከጥናቱ 3 የተለያዩ ውጤቶች ሊገኙ ይችላሉ።



### 1 ተስማሚ መጠለያ እናገኛለን

ክእርስዎ ጋር የሚሄድ መጠለያ ካገኘን፣ አሁንም እንድትመለሱ ውሳኔ ይደርስዎታል።

ወደ ቀኝ ይመልከቱ



### 2 እርስዎ ትብብር ኣድርገዋል፣ ነገር ግን መጠለያ ማግኘት አልቻልንም

እርስዎ እስከ ኣሁን ድረስ መጠለያ እንዲገኝሎት ትብብር ያደረጉ ከሆነ ነገር ግን ክእርስዎ ጋር የሚሄድ መጠለያ ካልተገኘ፣ ከዚያ ይህንን ወደ IND እናሳውቃለን። ከዚያም IND በኔዘርላንድ ውስጥ መቆየት እንደሚችሉ ሊወስን ይችላል።







### 3 እርስዎ በበቂ ሁኔታ አይተባበሩም፣ እናም መጠለያ ማግኘት አልቻልንም

እርስዎ ሁሉንም ነገር የማትነግሩን ከሆነ ወይም ሃቅ የማይናገሩ ከሆነ IND ተጨማሪ ምርመራ እንድናደርግ ሊጠይቀን ይችላል። አሁንም ለእርስዎ የሚሆን መጠለያ ልናገኝ ካልቻልን ዕድሜዎ 18 አመት ከሞሉ በኋላ በኔዘርላንድስ የሚኖርዎት ቆይታዎ ህገወጥ ይሆናል ማለት ነው። ከዚያ በኋላ መጠለያ እና ትምህርት የማግኘት መብት የለዎትም። እንዲሁም ደግሞ ኔዘርላንድስን ለቀው ለመውጣት ሊገደዱ ይችላሉ።



## እንድትመሰሉ ውሳኔ የተሰጥዎት ከሆነ

ኔዘርላንድስን መልቀቅ አለብዎት። ይህ ለእርስዎ ምን ማለት እንደሆነ እና ማን ትብብር እንደሚሰጥዎት እንነገራለን። 3 የተለያዩ ውጤቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

### 1 እርስዎ ትብብር ያደርጋሉ እና ትመለሳላችሁ

ከቤተሰብዎ፣ ከምታውቃቸው ሰዎች ወይም ከመጠለያው ስፍራ ጋር በጋራ ስምምነት እናደርጋለን። አስፈላጊ ከሆነ የጉዞ ሰነዶችን እናዘጋጃለን። ኣንድ ተባባሪ ሰው ደግሞ ክእርሱ ጋር እንድትኖሩ ፍቃደኛ ወደሆነ ሰው ይወስድዎታል።



በተቻለ መጠን ብዙ ከነገሩን እንረዳዎታለን። እንዲሁም ስልጠና ወይም ሥራ ሲፈልጉ እንረዳዎታለን።




### 2 እርስዎ ትብብር ያደርጋሉ ነገር ግን መውጣት አትችሉም።

እርስዎ ትብብር ቢያደርጉም፣ እርስዎን ይህንን ሃገር ለቀው እንዲወጡ ማድረግ ካልተቻለ ይህንን ወደ IND እናሳውቃለን። ከዚያም IND በኔዘርላንድ ውስጥ መቆየት እንደሚችሉ ሊወስን ይችላል።






### 3 እርስዎ በበቂ ሁኔታ አይተባበሩም፣ እና ክእርስዎ ጋር ጥሩ ስምምነቶችን ማድረግ አይቻልም

እርስዎ ሁሉንም ነገር የማትነግሩን ከሆነ ወይም ሃቅ የማይናገሩ ከሆነ፣ ያኔ ልንረዳዎ አንችልም። እርስዎን ይህንን ሃገር ለቀው እንዲወጡ ማድረግ ካልተቻለ ዕድሜዎ 18 አመት ከሞሉ በኋላ በኔዘርላንድስ የሚኖርዎት ቆይታዎ ህገወጥ ይሆናል ማለት ነው። ከዚያ በኋላ መጠለያ እና ትምህርት የማግኘት መብት የለዎትም። እንዲሁም ደግሞ ኔዘርላንድስን ለቀው ለመውጣት ሊገደዱ ይችላሉ።

Amhaars, 2024